ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ በመንግስት የልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/84 እና በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 74/85 የተቋቋመ የመንግስት የልማት ድርጅት ሲሆን አራት ቅርንጫፍ ፋብሪካዎች በስሩ ያቀፈ ሆኖ እነዚህ ፋብሪካዎች በተለያዩ ጊዜያት የተቋቋሙና በጂኦግራፊያዊ አቀማመጣቸው በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ናቸው፡-

እነርሱም፡-

- ሰበታቅ/ፋብሪካ(በ1898 ዓ.ም የተመሰረተ)
- ማይጨው ቀ/ፋብሪካ (በ1906 ዓ.ም የተመሰረተ የማምረቻ ፋብሪካው ወደ መካኒሳ የተጠቃለለ)
- አቃቂ ቅርንጫፍ ፋብሪካ(በ1930 ዓ.ም የተመሰረተ የማምረት ሂደቱን ያቆመ)
- መካኒሳ ቅ/ፋብሪካ (ዋና መስሪያ ቤት እና በ1949 ዓ.ም የተመሰረተ) በመባል ይታወቃል፡፡

እነዚህምፋብሪካዎችቀደምሲል በተለያዩ የግል ባለሃብቶች ስር ይተዳደሩ የነበሩ ሲሆን በ1969 ዓ.ም. በመንግስት ይዞታ ስር በአንድ ላይ ተጠቃለው "ብሔራዊአልኮልናአረቄ ፋብሪካ" የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የሰበታና መካኒሳ ቅርንጫፍ ፋብሪካዎች በከፍተኛ ወጪ አቅማቸውንና ዘመናዊነታቸውን በማሳደግ ቀድሞ ከነበረውአጠቃላይ የማምረት አቅማቸው ከአራት እጥፍ በላይ በማሳደግ በሙሉ የማምረት ሥራ ላይይገኛሉ፡፡ፋብሪካው በተለያዩ የአልኮል መጠጦች፣ንጹህ አልኮል እና እሳት አልኮል በማምረት ለደምበኞቹ እያሰራጨ የሚገኝ አንጋፋ ድርጅትነው፡፡

ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ የአልኮል መጠጦችን፣የንጹህ አልኮልና የእሳት አልኮል በጥራት አምርቶ በሀገር ውስጥና በውጭ ገበያ ያቀርባል፡፡በመሆኑም ፋብሪካው አሁን በሚያመርታቸው ምርቶች በሀገር ውስጥ ገበያ ጠብቆ የቆየውን መልካም ስምና ዝና በተለይም ጅምሩን የኤክስፖርት እንቅስቃሴ ከማጎልበት አኳያ እንዲሁም በአንጋፋ የአልኮል አምራችነቱ የጠነከረውን የማምረት ሥራ ልምድ አቀናጅቶ እየሰራ ነው፡፡

ድርጅቱ ውስጣዊና ውጫዊ አካባቢያዊ ሁኔታዎች በመገምገም የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ በማዘጋጀት ጥራት ያለው ምርትና አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ በደንበኞች ዘንድ መልካም ስም ያለውና በራሱ ገቢ የሚተዳደር አትራፊ ድርጅት ከመሆኑም በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት ለ518 ቋሚ፣ ለ25 ኮንትራት፣ለ141 ጊዜያዊ በፕሮጀክት እየሰሩ የሚገኙ እንዲሁምበኤጀንሲ አውት ሶርስ በተደረጉ ስራዎች ማለትም በጽዳት36፣ በጥበቃ128፣ በጫኝና አውራጅ100 በአጠቃላይ ለ948 ሰራተኞች የሥራ ዕድል ፈጥሯል:: ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካየ ተለያዩ የአሰራር ማሻሻያ ስራዎች ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን እነሱም የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት MIS፣ የጥራት ስራ አመራር ስርዓትISO 9001-2015፣ የአከባቢ ጥበቃ ስርዓት ISO 14001-2015፣ የላብራቶሪ ስራ አመራር ስርዓት ISO 17025-2005 ወ.ዘ.ተ.፡፡